DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የSY2020-23 የDCPS የቀን መቁጠሪያ (Calendar) FAQ

**DCPS የቀን መቁጠሪያውን (calendar) እንዴት ይቆጣጠራል?**

በቀለም ትምህርት ዓመቱ ውስጥ፣ DCPS ቢያንስ 180 የትምህርት መስጫ ቀናትን፤ እንዲሁም በርካታ ከትምህርት ቤት ውጪ የሆኑ ቀናትን የጊዜ ሰሌዳው ይይዛል፡፡ እነዚህ አብዛኛዎቹ ቀናት፣ በዲሲ የማዘጋጃ ቤት ደንቦች DCMR) ወይም የዋሽንግተን የአስተማሪዎች ማህበር (Washington Teachers' Union (WTU) የጥቅል መደራደሪያ ስምምነት (CBA) ድንጋጌዎች ምክንያት አስገዳጅ (mandatory) ናቸው፡፡ እነዚህ መስፈርቶች ለማስፈጸም ቃል ከተገባ በኋላ፣ DCPS የቶቹን ቀናት በቀን መቁጠሪያ ላይ የማስገባት ውስን በሆነ ተለዋዋጭነት ሲኖራቸው፣ ሆኖም ግን፣ እነዚህ ቀናት መቼ ሊሆኑ እንደሚችሉ፣ በቀን መቁጠሪያው ላይ መለዋወጥ ይችላል፡፡ በDCMR እና በWTU CBA መስፈርቶች መሠረት እና ከቀደሙት ዓመታት ከማህበረሰቡ የተገኙ አስተያየቶችንም ጨምሮ፣ የDCPS የመሪዎች ኮሚቴ፣ የDCPSን የቀን መቁጠሪያ (calendar) ረቂቅ ሃሳብን የያዘ፣ ረቂቅ (draft) በማዘጋጀት እና የመጨረሻውን ማስተካከያ ለማድረግ የሕዝብን አስተያየት ይጠይቃል፡፡ ኮሚቴው የተለያዩ ባለድርሻ አካላት (stakeholders) ፍላጎቶች በማመጣጠን፣ ሁሉም የተሰጡትን ድምፆች እኩል የሆነ አመለካከት እንደተሰጣቸው ለማረጋገጥ ጠንክሮ ይሰራል፡፡

**ከዲሲ ማዘጋጃ ቤት ደንቦች (DC Municipal Regulations (DCMR) ምን ይፈለጋል?**

DCMR፣ ከ180-185 የተማሪ ቀናት[1] እና የመንግስት ሠራተኞች የሚከተሏቸውን የበዓል (holiday) ቀናትን በሙሉ እንዲያገኙ ይጠይቃል:

- Labor Day, በSeptember ወር፣ የመጀመሪያው ሰኞ
- Columbus Day, በOctober ወር፣ ሁለተኛው ሰኞ
- Veterans Day, November 11
- Thanksgiving Day, በNovember ወር፣ አራተኛው ሐሙስ
- Christmas Day, December 25
- New Year's Day, January 1
- Martin Luther King, Jr. Day, በJanuary ወር፣ ሶስተኛው ሰኞ
- Inauguration Day, January 20 (በየአራት ዓመት)
- President's Day, በFebruary ወር፣ ሶስተኛው ሰኞ
- District of Columbia Emancipation Day, April 16
- Memorial Day, በMay ወር፣ የመጨረሻው ሰኞ
- Independence Day, July 4
- *ማስታወሻ: ሕጋዊ የሆነ በዓል ቅዳሜ ቀን ከሆነ፣ ከዚያ ቀን በፊት ያለው ዓርብ ቀን ሕጋዊ የሕዝብ በዓል ሆኖ የሚውል እና ሕጋዊ የሆነው በዓል እሁድ እለት ከዋለ፣ ከዚያ ቀን በኋላ ያለው ሰኞ፣ ሕጋዊ የሕዝብ በዓል ሆኖ ይውላል፡፡*[2]

DCMR፣ ቢያንስ የ6 ሰዓት ርዝመት ያለው፣ እስከ 185 መደበኛ የሆነ የትምህርት መስጫ ቀናትን ያልበለጠ ትምህርት ተማሪዎች እንዲያገኙም ይጠይቃል፡፡[3] በተጨማሪም፣ የቀለም ትምህርቱ በሚካሄድበት ዓመት ሙሉ፣ ተማሪዎችን የ120 ሰዓት (ወይም፣ በግማሽ ዓመት ከሆነ ደግሞ - 60 ሰዓት)[4] የክፍል ውስጥ የትምህርት አሰጣጥ እንዲያገኙ፣ DCMR የ'ካርኒጊ ዩኒት' (Carnegie Unit) መስፈርቶችን ለይቶ ይገልፃል፡፡ DCPS ቢያንስ የ44 ቀናት ትምህርት በአንድ በተርም (term) በማካሄድ፣ ተፈላጊ የሆነውን የተርም (term) የትምህርት አሰጣጥ ሰዓቶች ለማግኘት ያመጣጥናል፡፡

**ከ'ዋሽንግተን የአስተማሪዎች ማህበር (WTU) Washington Teachers' Union (WTU)፣ የጥቅል መደራደሪያ ስምምነት Collective Bargaining Agreement (CBA) የሚፈለገው ምንድነው?**

---

[1] DCMR Section 5-A 2806.1

[2] Title XII of the District of Columbia Government Comprehensive Merit Personnel Act of 1978 (CMPA) Section 1220.1

[3] DCMR Section 5-A 2806.2

[4] DCMR Section 5-A 2299.1

WTU CBA፣ ከ196 የስራ ቀናት[5] ያልበለጠ፣ 10-ወራትን ከአስተማሪዎች ይጠብቃል፡፡ በተጨማሪም፣ ቢያንስ 10 የሙያ ማሳደጊያ ቀናቶችን[6] እና በእያንዳንዱ ተርም (term)[7] መጨረሻ ላይ፣ የግማሽ ቀን የመዝገብ አያያዝ ቀን ይጠይቃል፡፡ CBA፣ እስከ ሶስት (3) ትምህርት የማይሰጥባቸው ቀናት (non-instructional days) እና አንድ (1) ወደ-ትምህርት ቤት-መመለሻ ምሽትን (Back-to-School night)[8] ጨምሮ፣ እስከ አራት የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎችን ይፈቅዳል፡፡

**በየዓመቱ የትምህርት ቤት የመጀመሪያ ቀን የሚሆነው፣ የAugust ወር የመጨረሻ ሰኞ ቀን የሚሆነው ለምንድን ነው?**

የባለድርሻ አካላት (Stakeholder) ምላሽ (feedback)፣ ላለፉት በርካታ ዓመታት ውስጥ የመጀመሪያ የምርጫ ቀናትን በጥቅሉ ሲቀርብ ቆይቷል፡፡ ሆኖም በርካታ የDCPS ወላጆች፣ የትምህርት ዓመቱ ቀደም ብሎ እንዲጀመር ሲከራከሩ ቆይተዋል፤ በርካታ የስራ ባልደረቦችም ቀን ወደኋላ ለመግፋት እና ከ“Labor Day” በኋላ ለማድረግ፣ ከሌሎች በዙሪያው ከሚገኙ የመኖሪያ ግዛት ሥልጣን ጋር፣ ወጥነት ባለው ሁኔታ እንዲሰሩ ሲጠይቁ ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ባለው ዓመት (SY19-20)፣ DCPS ትምህርት የጀመረው በAugust ወር የመጨረሻ ሰኞ ሲሆን፣ በእነዚሁ ሁለት የባለድርሻ ቡድኖች መካከል ያለውን ልዩነት ለመለየት ጥረት በማድረግ፣ እና ወጥነት እንዲኖረው በማሰብ፣ DCPS በAugust ወር የመጨረሻውን ሰኞ፣ የመጀመሪያ ቀን በማድረግ ለሚቀጥሉት ሶስት አመታት ይቆያል፡፡

**DCPS እንዴት ነው የሕዝብን ምላሽ (feedback)ን መጠየቅ የቻለው?**

የDCPS ሠራተኞች፣ የቀን መቁጠሪያ (calendar) ረቂቅ እቅድ መስጫን በማካፈል፣ ከበርካታ የጉባኤ አባላቶች፣ የቻንስለሩን ርዕሰ መምህር እና የአስተማሪ አማካሪ ቦርዶችን (Teacher Advisory Boards)፣ ጨምሮ በርካታ ሳምንታትን አሳልፈዋል፡፡ DCPSም በበኩሉ፣ ከሁሉም የማህበረሰብ አባላት፣ DCPS ድህረ-ገጽን በመጠቀም ባስቀመጠው ግልጽ በሆነ የዳሰሳ ጥናት አማካኝነት፣ ምላሽ (feedback)ን ይጋብዛል፡፡ DCPS፣ ርዕሰ መምህር፣ የዳሰሳ ጥናቱን ከማህበረሰባቸው ጋር እንዲያጋሩ እና በDCPS ማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት እና በሌላ የኦንላይን መድረኮች (ለምሳሌ፤ ኔክስትዶር (NextDoor) በመሳሰሉት አማካኝነት ያስተዋውቃል፡፡ ከ3,000 በላይ የሚሆኑ ወላጆች፣ አስተማሪዎች፣ እና የማህበረሰብ አባላት፣ እያንዳንዱን በDCPS የሚገኝ ትምህርት ቤትን በመወከል በእቅድ መስጫው ላይ ምላሻቸውን (feedback) አካፍለዋል፡፡

**የሕዝብ ምላሽ (feedback) ምንን ያመለክታል?**

DCPS ከቀድሞ የተለምዶ አሰራር የሚያስወጡ ለውጦች ሲኖሩ እና እርምጃ ለመውሰድ፣ DCPS ሙሉ ነፃነት ባለው ነገሮች ላይ እንኳን፣ የማህበረሰቡን ምላሽ (feedback) ልዩ ጥንቃቄ ሰጥቶ የሚመለከተው ይሆናል። ስለሆነም፣ የምላሽ የዳሰሳ ጥናቱ ጥቂት ቁልፍ የሆኑ ገፅታዎች ላይ ትኩረት የሚሰጣቸው: የምርጫ ቀናት (Election Days)፣ የእረፍት ጊዜያት (Breaks)፣ የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎች (Parent-Teacher Conferences (PTC)፣ እና የሙያ ማሳደጊያ (Professional Development (PD)።

የእያንዳንዱ ገፅታ፣ ቁልፍ የሆኑ ተሞክሮዎች እንደሚከተለው ነው:

- **የምርጫ ቀናት:** 85.7% ምላሽ ሰጪዎች፣ DCPS የምርጫ ቀናት እንደ ትምህርት የማይሰጥባቸው ቀናት በመሆን፣ ለተማሪዎች፣ እና ለወላጅም ሆነ አስተማሪዎች የበዓል ቀን ሆኖ እንዲቀጥል ምርጫቸው እንደሆነ አሳውቀዋል፡፡ ሆኖም ግን (55.5.%) የሚሆኑት አብዛኛዎቹ ምላሽ ሰጪዎች፣ ከምርጫ በፊት ቀናትን እንደ አጠቃላይ የምርጫ ቀናት ከመመልከት ይልቅ እንደ የትምህርት ቀናትን ሆነው እንዲቀጥሉ ምርጫቸው ነው፡፡
- **የእረፍት ቀናት (Breaks):**
  - **የምስጋና ቀን (Thanksgiving):** (80%) ምላሽ ሰጪዎች የሶስት ቀናት የምስጋና ቀን (Thanksgiving) በዓል እንዲሆን ጠንካራ ምርጫ አላቸው።

---

[5] Washington Teacher’s Union, Collective Bargaining Agreement (Oct.1, 2016-September 30, 2019) Article 23, Section 23.1.1.2

[6] Washington Teacher’s Union, Collective Bargaining Agreement (Oct.1, 2016-September 30, 2019) Article 2, Section 2.6.1

[7] Washington Teacher’s Union, Collective Bargaining Agreement (Oct.1, 2016-September 30, 2019) Article 19, Section 19.3

[8] Washington Teacher’s Union, Collective Bargaining Agreement (Oct.1, 2016-September 30, 2019) Article 23, Section 23.9

- **የክረምት እረፍት (Winter Break):** ወደ ግማሽ የሚጠጉ ሁሉም ምላሽ ሰጪዎች፣ የክረምት እረፍት፣ በረቂቅ ሐሳቡ ላይ እንደተካተተው፣ (ስምንት ቀናት በSY20-21፣ ሰባት ቀናት በSY21-22፣ እና ስምንት ቀናት በSY22-23) እንዲሆን ምርጫቸው ነው።
- **የየካቲት ወር እረፍት (Break February):** አነስተኛ ብዛት ያላቸው (54.5%)፣ በSY20-21 የየካቲት ወር እረፍት (February Break) እንዲጨመር የሚሚገቱ ሲሆን፣ ከዚያ እጅግ የሚበዛው ደግሞ (68.2%)፣ በSY21-22 እና በSY22-23፣ የየካቲት ወር እረፍት (February Break) በዚያው ለማቆየት ይሚገታሉ፡፡ የየካቲት ወር እረፍት (February Break)፣ በግልጽ ምላሽ አሰጣጥ ላይ በጣም ወሳኝ የሆነ ርዕስ በመሆን፣ ከ300 በላይ ምላሽ ሰጪዎች የእረፍት ጊዜውን እንዳለ ለመቀጠል ሲከራከሩ፣ አብዛኛዎች ደግሞ በግልጽነት እረፍቱ፣ 'አንድ ሙሉ ሳምንት' እንዲሆን ይከራከራሉ፡፡
- **የፀደይ ወራት እረፍት (Spring Break):** ወደ 65% የሚጠጋው ምላሽ ሰጪ፣ DCPS የፀደይ ወራት እረፍትን (spring break) ከዲሲ የነፃነት ቀን (DC Emancipation Day) ጎን ለጎን እንዲከበር በቀረበው ሃሳብ መሰረት እንዲቀጥል ምርጫቸው እንደሆነ ይገልጻሉ።

* **የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎች (Parent-Teacher Conferences (PTC):** አብዛኛዎቹ፣ (65.1%) ምላሽ ሰጪዎች፣ DCPS ሁለት የPTCዎችን በየዓመቱ እንዲያደርግ ምርጫቸው ነው። አብዛኛዎቹ ምልሽ ሰጪዎች፣ ግልፅ የምላሽ ጥያቄን ሲመልሱ፣ PTC ከPD በፊት እንዲሆንላቸው የሚመርጡ እንደሆነ እና ሁለቱም አብረው በሚጣመሩበት ጊዜ፣ ቤተሰቦች ቅዳሜና እሁድ እንዲጓዙ እና አስተማሪዎች ደግሞ ከPTC በኋላ ትምህርት የሌለበት ቀን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።
* **የሙያ ማሳደጊያ (Professional Development):** 50% የሚሆኑ ምላሽ ሰጪዎች፣ DCPS ቅድመ-አገልግሎትን ከማራዘም ይልቅ፣ በዓመት ውስጥ ሶስት በመላው-ዲስትሪክ የሚሰጥ የPD ቀናትን እንዲኖር መቀጠሉ ምርጫቸው እንደሆነ ገልጸዋል።

**DCPS የሕዝብ ምላሽ ላይ በመመርኮዝ፣ በቀን መቁጠሪያው (calendar) ላይ ምን ዓይነት ማስተካከያ አድርጓል?**

ሃሳብ መስጫው የቀን መቁጠሪያ (calendar) ላይ የተሰጠው የሕዝብ ምላሽ፣ በጠቅላላው፣ የወቅቱን ቀን መቁጠሪያ አሰራርን የሚደግፍ ነው፡፡ ሆኖም፣ DCPS የቀን መቁጠሪያውን (calendar) ከሕዝብ የተሰጠን ምላሽ የሃሳብ መስጫን በመመርኮዝ የሚከተሉትን ማስተካከያዎች አድርጓል:

* DCPS 6[ተኛውን] ቀን የቅድመ-አገልግሎት በሃሳብ መስጫው ዝርዝር ላይ አሁን ባለበት ሁኔታ ያቆየዋል፡፡ ነገር ግን፣ DCPS ይህ ቀን ለአስተማሪዎች የክፍል-ውስጥ ዝግጅት እንዲውል፣ ለትምህርት ቤቶች ግልጽ የሆነ መመሪያን ያስተላልፋል።
* DCPS በዓመት ከሚደረገው የወላጅ አስተማሪ ሶስት ስብሰባዎች ወደ ሁለት እንዲቀየር እና የPTCs እና PD አሰጣጥን በተመለከተ፣ PTCs ሐሙስ ቀን ላይ እንዲውል ተደርገው፣ PD ደግሞ አርብ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡
* በSY20-21፣ DCPS አጭር የየካቲት ወር እረፍት (February Break) አድርጎ፣ በSY21-22 እና SY22-23፣ የየካቲት ወር እረፍት (February Break) ወደሙሉ ሳምንት እንዲራዘም ያደርጋል፡፡ ይህ አነስተኛ ማስተካከያ እንዲደረግና፣ በተርሙ (term) ውስጥ ያሉትን ቀናት ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ለማስተካከል፣ በዓመቱ መጨረሻ፣ ለተማሪዎች አንድ ተጨማሪ ቀን እንዲጨመር አስፈላጊ አድርጎታል፡፡

**ለምንድነው DCPS የሐይማኖት በዓላትን ለተማሪዎች ትምህርት-የማይሰጥባቸው ቀናት አድርጎ ያላካተተው?**

የበርካታ እምነት ተካታዮች በሚገኙበት በDCPS ማህበረሰብ ውስጥ፣ ሁሉንም DCMR-የሚፈቅዳቸውን በዓላት እና የሐይማኖት በዓላት፣ እንደ ትምህርት-የማይሰጥባቸው ቀናት አድርጎ ማስገባት ሊሰራ የማይችል ነገር ነው። ይህ በእንዲህ እያለ፣ በተቻለ መጠን፣ ለሰራተኞች እና ተማሪዎች፣ በነዚህ ቀናት እጅግ አስፈላጊ ነገሮችን (ማለትም፤ ፈተና፣ የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባ፣ PD ቀናትንና ወዘተ) የጊዜ ሰሌዳን፣ ዋነኛ በሆኑ የሐይማኖት በዓላት ቀን እንዳይደረጉ በማድረግ፣ በነዚህ ቀናት ተማሪዎች እና የስራ ባልደረቦች፣ ምንም ዓይነት ጉልህ ችግር በማይፈጥር ሁኔታ ፈቃድ ጠይቀው እንዲቀሩ ለማድረግ ስለምንፈልግ ነው፡፡ DCPS የተማሪዎችን እና የስራ ባልደረቦችን ሐይማኖታቸውን እንዲያከብሩ እና ተማሪዎች እና ሠራተኞች የሐይማኖት በዓላቸውን ለማክበር የእረፍት ቀን መሙላታቸውን አክብሮ ይቀበላል።

**DCPS የትምህርት ዓመቱን አራዝሟል?**

የለም፣ የDCPS ተማሪዎች በዓመት የ180 የትምህርት አሰጣጥ ቀናትን ማግኘታቸውን ይቀጥላሉ። በኦገስት (August) መጨረሻ ትምህርት መጀመርን እና የየካቲት ወር እረፍት (February Break) መጨመርን ታሳቢ በማድረግ፣ DCPS ከሌሎች በዲስትሪክቱ አጎራባቾች በተለየ ሁኔታ፣ በጁን (June) ወደ መጨረሻው ገደማ መጨረስ አለበት። ሆኖም፣ የተማሪዎች ጠቅላላ ቀናት እና የ10-ወራት ተቀጣሪዎች፣ ከዚህ ቀደም ከነበሩ ዓመታት ጋር ወጥነት ይታይባቸዋል፡፡

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

**በየዓመቱ የምርቃት የጊዜ ክፍተት መቼ ላይ ይውላል?**
ለSY20-21 ሲኒየሮች (seniors’) የመጨረሻ ቀን አርብ ጁን 11፣ (June 11) ይሆንና፤ የምርቃት ስነስርዓቱ ከቅዳሜ፣ ጁን 19 (June 19) እና ሐሙስ፣ ጁን 24 (June 24) መካከል ባለው ቀን ውስጥ ይውላል፡፡

ለ SY 21-22 ሲኒየሮች (seniors’) የመጨረሻ ቀን አርብ ጁን 10፣ (June 10) ይሆንና፤ የምርቃት ስነስርዓቱ ከአርብ፣ ጁን 17 (June 17) እና እሮብ፣ ጁን 22 (June 22) መካከል ባለው ቀን ውስጥ ይውላል፡፡

ለ SY 22-23 ሲኒየሮች (seniors’) የመጨረሻ ቀን አርብ ጁን 9፣ (June 9) ይሆንና፤ የምርቃት ስነስርዓቱ ከቅዳሜ፣ ጁን 17 (June 17) እና ሐሙስ፣ ጁን 22 (June 22) መካከል ባለው ቀን ውስጥ ይውላል፡፡

**ለ11-ወር ሠራተኞች የመጀመሪያ እና መጨረሻ ቀናት የቶቹ ናቸው?**
ለ11-ወር ተቀጣሪ ሥራ ባለደረባ አባላት፣ በመጪው ሶስት የትምህርት ቤት ዓመታት ውስጥ፣ የመጀመሪያና የመጨረሻ በስራ ቦታ የመገኛ ቀናት ለመወሰን፣ አሁንም በምልከታ ላይ ይገኛል። ቀናቱ አንድጊዜ የመጨረሻ ውሳኔን ካገኙ በኋላ፣ ለሠራተኞች በቀጥታ የሚገለጽ እና በተገቢው የዜና ማሰራጫ ወረቀት ይካተታል።